ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ በተመለከተ የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን በይግባኝ አይቶ ፈጣን፣ ውጤታማና ፍትሃዊ ውሳኔ በመስጠት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ማስቀረት የሚያስችል የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደገና ማቋቋም እና አደረጃጀትና አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፩/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፲፰ በተደነገገው መሠረት የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ እንደገና ለማቋቋም ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፲፫/፪ሺ፲፰ ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪.ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፡-

፩. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. "ምክር ቤት" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ነው፤

፫. "ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤

**WHEREAS**, it has become necessary to re-establish an appeal hearing council and set up its organization and procedures to review administrative decisions regarding land holding expropriation for public purposes, compensation payment, and resettlement upon an appeal made, thereby providing swift, effective, and fair decisions to solve challenges of good governance;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 18 of Proclamation Number 1161/2019 that determine the conditions for land holding expropriation for public purposes, compensation payment, and resettlement of displaced persons, the Addis Ababa City Council has issued this Regulation to re-establish the land holding expropriation and compensation matters appeal hearing council.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as: "The Addis Ababa City Government Land Holding Expropriation and Compensation Matters Appeal Hearing Council Re-Establishment Regulation Number 13/2026."

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City Government"** means the Addis Ababa City Administration;
2. **"Council"** means the Addis Ababa City Council;
3. **"Mayor"** means the Addis Ababa City Mayor;

፬. "አዋጅ ወይም ደንብ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፩/፪ሺ፲፩ ወይም ደንብ ቁጥር ፬፻፸፪/፪ሺ፲፪ ነው፤

፭. "አቤቱታ ሰሚ ጉባዔ" ማለት በምክር ቤቱ ደንብ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፪ የተቋቋመ የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ ጉባዔ ነው፤

፮. "ዳኛ" ማለት የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ዳኛ ነው፤

፯. "ሬጅስትራር" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ እና በሌሎችም ድንጋጌዎች የተሰጡትን ተግባራት የሚያከናውን የይግባኝ ሰሚው ቋሚ ሠራተኛ ነው፤

፰. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፱. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ጉባዔው መቋቋም፣ አደረጃጀት እና ስለዳኞች

### ፫. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" ተብሎ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለዉ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪. የጉባዔው ተጠሪነት ለምክር ቤቱ ነው።

4. **"Proclamation or Regulation"** means Proclamation No. 1161/2019 or Regulation No. 472/2020, respectively, that were issued to determine the conditions for land holding expropriation for public purposes, compensation payment, and resettlement of displaced persons;

5. **"Complaint Hearing Council"** means the land holding expropriation and compensation matters complaint hearing council that was established under Regulation No. 6/2020 of the Council;

6. **"Judge"** means a judge of the land holding expropriation and compensation matters appeal hearing council;

7. **"Registrar"** means a permanent employee of the appeal council who carries out the duties specified under Article 17 of this Regulation and other provisions;

8. **"Person"** means any natural or juridical person;

9. In this **Regulation**, any expression in the masculine gender shall apply to the feminine.

## PART TWO
## ESTABLISHMENT, ORGANIZATION, AND JUDGES OF THE COUNCIL

### 3. Establishment

1. The Addis Ababa City Government Land Holding Expropriation and Compensation Matters Appeal Hearing Council (hereinafter the **"Council"**) is hereby re-established by this Regulation as an autonomous organ having its own legal personality;
2. The Council shall be accountable to the City Council.

፮. በቃለ ጉባዔ የሚያዙ ወይም በውሳኔ ውስጥ የሚመዘገቡ የቃል ወይም የጽሁፍ ክርክሮች ሁሉ በሚገባ መያዛቸውንና መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፤

፯. የጉባዔውን ጽሕፈት ቤት መዋቅር በማዘጋጀት ለከተማ አስተዳዳሩ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት አስተዳዳር ቢሮ አቅርቦ ያስፀድቃል፤

፰. በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ያሰናብታል፤

፱. የጉባዔውን ጽህፈት ቤት በጀትና ዕቅድ በማዘጋጀት ለከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ ቢሮ ያቀርባል፤

፲. ለጉባዔው የተፈቀደውን በጀት ያስተዳድራል፤ በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ ሕግ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

፲፩. የዕቅድና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፲፪. ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ የሥራ ግንኙነት ጉባዔውን ይወክላል፤

፲፫. ፕሬዚዳንቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለጉባዔው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ፕሬዚዳንቱ ወይም ለጉባዔው ጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

፲፬. የጉባዔውን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፯. <u>የምክትል ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባር</u>

፩. ፕሬዝዳንቱ በሌለ ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

፪. በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡት ሌሎች ሥራዎችን ይሠራል፡፡

6. Ensure that all oral or written arguments recorded in minutes or judgments are properly documented and prepared;
7. Prepare the organizational structure of the secretariat of the council and submit it to the public service and human resource development bureau of the city administration for approval;
8. Hire, administer, and dismiss the civil servants of the secretariat in accordance with the civil servants' laws of the city administration;
9. Prepare the budget and plan of the secretariat of the council and submit it to the finance bureau of the city administration;
10. Administer the approved budget of the council; effect payments as per the financial laws of the city administration;
11. Prepare the plan and budget performance report of the council and submit same to the relevant organ;
12. Represent the council in all its dealings with third parties;
13. The president may delegate part of his powers and duties to the vice president or other officers of the secretariat of the council to the extent necessary for the effective performance of the activities of the council.
14. Carry out other activities to attain the objectives of the council.

7. <u>**Power and Duties of the Vice President**</u>

1. Act on behalf of the President in his absence;
2. Carry out other activities that are specifically designated by the President.

## ፰. ስለጉባዔው ዳኞች

፩. ጉባዔው አምስት አባላት የሚኖሩት ሲሆን ከአባላቱ መካከል ፕሬዝዳንቱ የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፤ እርሱ በማይኖርበት ወቅት ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሰብሳቢ ይሆናል፤

፪. ከጉባዔው ዳኞች መካከል ሦስቱ ብቃትና ልምድ ያላቸው የሕግ ባለሙያዎች ሲሆኑ ሁለቱ አግባብ ካለው ሌላ የሙያ ዘርፍ የሚሾሙ ይሆናሉ፤ ሆኖም ከሦስቱ አባላት መካከል ቢያንስ አንዷ ሴት መሆን ይኖርባታል፤

፫. ማንኛውም የጉባዔ ዳኛ በዚህ ደንብ መሰረት ግዴታውን በአግባቡ ለመወጣት ሲል በፈጸመው ድርጊት ወይም ባለማድረጉ ምክንያት የወንጀል ክስ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

## ፱. የጉባዔው የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት

፩. ከጉባዔው ዳኞች መካከል አንዱ የሕግ ባለሙያ ሆኖ ሦስቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

፪. ጉባዔው በቀረቡለት የይግባኝ ጉዳዮች ላይ በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ድምጽ በእኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

፫. በሃሳብ የተለየ የጉባዔ ዳኛ የሃሳብ ልዩነቱን በውሳኔ ላይ በጽሁፍ ያሰፍራል፡፡

## ፲. የዳኛ መመልመያ መስፈርት

ማንኛውም ሰው የጉባዔ ዳኛ ሆኖ ለመሾም የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

## 8. About Judges of the Council

1. The Council shall consist of five members, among whom the President shall serve as a chairperson; where in the absence of the President, the Vice President shall act as a chairperson;
2. Three of the Council Judges shall be qualified and experienced legal professionals, while the other two shall be appointed from other relevant professional fields; provided, however, that at least one of the three legal members must be female;
3. No Council Judge may be subjected to criminal charges for actions performed or omitted in good faith while properly discharging his duties under this Regulation.

## 9. Decision-Making Procedure of the Council

1. There shall be a quorum where three of the judges of the council are present, and at least one of them must be a lawyer;
2. The Council shall pass decisions on appealed cases by a majority vote; and in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
3. A dissenting Judge shall record his dissenting opinion in writing within the decision.

## 10. Criteria for Selecting Judges

Any person must meet the following criteria to be appointed as a judge for the council:

፩. እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም አግባብነት ባለው የሙያ ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው፤

፪. ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ የሆነ፤

፫. የጉባዔው ዳኛ ሆኖ ለመስራት ሙሉ ፈቃደኛ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የሥነ-ምግባር ሁኔታውን የሚገልጽ ማስረጃ እና ሠራተኛ ከሆነ ከሚሰራበት መሥሪያ ቤት የሥራ መልቀቂያ ማቅረብ የሚችል፤

፬. በታታሪነቱ፣ በፍትሃዊነቱና በቅንነቱ መልካም ስም ያለው፤

፭. ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ለመሥራት ቁርጠኝነት ያለው፤

፮. ዕድሜው ፳፭ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፤

፯. ዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፡፡

## ፲፩. ቃለ መሃላ

፩. ማንኛውም የጉባዔው አባል ተሹሞ ሥራ ከመጀመሩ በፊት እንደሹመቱ በምክር ቤት ወይም በጉባዔው ፕሬዝዳንት ፊት በአካል ቀርቦ የሚከተለውን ቃለ መሃላ መፈጸም አለበት፤

፪. "እኔ ------------------------ በዛሬው እለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ማስለቀቅና ካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ዳኛ ሆኜ ተሹሜ ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነትና እምነት ለሕገ መንግሥቱ እና ለሕግ ብቻ ተገዢ በመሆን ስራው የሚፈልገውን ከፍተኛ ተነሳሽነት እና ሥነ-ምግባር በመላበስ ለማገልገል ቃል እገባለሁ።

1. Has at least a first (bachelor's) degree in a relevant field of study from a recognized higher education institution;
2. Loyal to the Constitution;
3. Confirm his absolute willingness to serve as a the council's judge, provide proof of good ethical conduct, and, if currently employed, present a letter of resignation from his employing office;
4. Possess a good reputation for diligence, fairness, and integrity;
5. Demonstrate commitment to working independently and impartially;
6. Be 25 years of age or above that;
7. Be an Ethiopian citizen.

## 11. Oath

1. Any member of the Council, prior to assuming office, shall appear in person before the city council or the President of the council, according to his status of appointment, and take the following oath:
2. "I, ------------------------, having been appointed today as a Judge of the Addis Ababa City Administration Land Holding Expropriation and Compensation Matters Appeal Hearing Council, do solemnly swear to discharge the highest responsibility and trust imposed upon me by being subject only to the Constitution and the Law, and serving with the highest level of motivation and ethics required by the role."

**፲፪.የዳኛ ከችሎት መነሳት**

ማንኛውም የጉባዔው ዳኛ በሚከተሉት ምክንያቶች ከጉዳይ ሊነሳ ይገባል፡-

፩. ከጉዳዩ ተከራካሪ ወይም ጠበቃ ጋር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ካለው፣

፪. ጉዳዩን ቀድሞ በዳኝነት ወይም በዕርቅ መንገድ ያየው ከሆነ፣

፫. ከጉዳዩ ተከራካሪ ወይም ከጠበቃው ጋር በሌላ ፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ያለው ከሆነ፣

፬. ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የማያስችል ሌላ ማንኛውም ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ካለ።

**፲፫.ከዳኝነት ስለ መሰናበት**

ማንኛውም የጉባዔ ዳኛ በሚከተሉት ምክንያቶች ከዳኝነት ሊሰናበት ይችላል፡-

፩. የሥነ-ምግባር ጥሰት ፈጽሞ ወይም በችሎታ ማነስ ወይም በሥራ አፈጻጸም ጉድለት ምክንያት እንደአግባቡ በምክር ቤቱ እንዲሰናበት ከተወሰነ፣

፪. የሥራ ኃላፊነቱን እንዳይወጣ በሚያደርግ የጤና እክል ምክንያት፣

፫. ራሱ ከዳኝነት በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ሲወስን፣

፬. በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሲደርስ፡፡

**፲፬. ስለ ጉባዔው ዳኞች ደመዎዝና ጥቅማጥቅም**

ለጉባዔ ዳኞች የሚከፈለው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከሥራው ክብደትና ባህሪ እንጻር የከተማውን አስተዳደር የፋይናንስ አቅም በማገናዘብ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ አጥንቶ ለከንቲባ ያቀርባል፣ በካቢኔ ሲወሰን ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

**12. Recusal of a Judge**

Any judge of the council shall recuse himself from a case for the following reasons:

1. If he has a relation by blood or marriage with a litigant or an attorney;
2. If he previously examine the case in a judicial capacity or through conciliation;
3. If he´has a pending litigation against a party or the attorney in another court;
4. If there exists any other improper condition that prevents the rendering of proper justice.

**13. Dismissal of a Judge**

Any judge of the council may be removed from his judicial capacity for the following reasons:

1. If decided by the city council due to ethical violations, incompetence, or performance deficiencies, as per the context;
2. Due to health issues that prevent him from discharging his duties and responsibilities;
3. When resigning voluntarily from judicial service;
4. Upon reaching the retirement age specified under the pension laws of civil servants.

**14. Salary and Benefits of the Council's Judges**

The public service and human resource development bureau shall study the salary and benefits to be paid for the council's judges by taking the weight and nature of the activities and the financial capacity of the city administration into consideration and submit same to the Mayor; implement it upon its approval by the cabinet.

## ክፍል ሦስት

## የጉባዔው አሰራር ሥነ-ሥርዓት

### ፲፭. የጉባዔው አሰራር

፩. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቅሬታ አቅራቢዉ ቅሬታዉን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፤

፪. ጉባዔው የሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ግራ ቀኝ ኮፒ አድርጎ መውሰድ ይችላሉ፤

፫. ማንኛውም በጉባዔው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል፤

፬. ጉባዔው የሚሰጣቸው ትዕዛዞችና ውሳኔዎች እንደ ማናቸውም የፍትሐብሔር ፍርድ ቤት ትዕዛዞች እና ውሳኔዎች ይቆጠራሉ፡፡

### ፲፮.የይግባኝ አቤቱታ አቀራረብ

፩. ይግባኝ አቤቱታው በባለጉዳይ ወይም በህጋዊ ወኪሉ ሊቀርብ ይችላል፤

፪. ይግባኝ የሚቀርበው በግልጽና እንዲታረም የሚፈልገውን ነገር ዝርዝርና የሚጠይቀውን ዳኝነት ዓይነት በመግለጽ ይሆናል፤

፫. የይግባኝ አቤቱታ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የተከራካሪዎቹን ስምና አድራሻ፤

ለ) ውሳኔውን የሰጠው አቤቱታ ሰሚ ጉባዔ ስምና አድራሻ፡

ሐ) የመዝገብ ቁጥር፤ ውሳኔ የተሰጠበት ቀን እና የጉዳዩን አጭር መግለጫ፤

መ) የይግባኙን ምክንያት እና የሚጠይቀውን ዳኝነት በግልጽ የሚገልጽ መግለጫ፤



## PART THREE

## WORKING PROCEDURE OF THE COUNCIL

### 15. Procedures of the Council

1. The appeal hearing council must make its decision within 30 days from the date the appellant submits his complaint;
2. Both parties in the lawsuit may obtain copies of orders or decisions made by the Council;
3. Any person who is dissatisfied with the decision of the council may lodge his appeal to the competent court;
4. Orders and decisions made by the council shall be regarded as orders and decisions of any civil court.

### 16. Submission of Appeal Petitions

1. An appeal petition may be lodged by the client himself or through his legal agent;
2. An appeal shall be submitted clearly, detailing the specific remedies sought and stating the type of adjudication requested;
3. An appeal application must include the following:
   - A. The name and address of the litigants;
   - B. The name and address of the complaint hearing council that made the decision;
   - C. The file number, the date on which the decision was made, and a brief description of the matter;
   - D. A clear statement specifying the grounds for the appeal and the adjudication sought;

ሠ) በአቤቱታ ሰሚ ጉባዔ የተሰጠውን የክርክር ሂደትና የውሳኔ ሙሉ ሰነድ (አቤቱታን፣ መልስንና ማስረጃዎችን ጨምሮ) በማልባጭ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ማቅረብ ይኖርበታል፤

፬. አቤቱታውን ያቀረበው ሰው አቤቱታው በእውነት የቀረበ ስለመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት ማረጋገጥ አለበት፤

፭. ጉባዔው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎችንም ይቀበላል።

## ፲፯. የሬጅስትራር ሚና

፩. ሬጅስትራሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሰረት የቀረበውን ይግባኝ በሚከተሉት መመዘኛዎች መሰረት ተሟልቶ የቀረበ ይግባኝ ስለመሆኑ ያጣራል፡-

ሀ) የይግባኙ መስፈርቶች የተሟሉ ስለመሆኑ፤

ለ) ይግባኙ በአዋጁ እና በደንቡ በተደነገገው የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ የቀረበ መሆኑን፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ይግባኙ እንዲከፈትለት የሚጠይቅ የፈቃድ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፤ ጉባዔው የቀረበለትን የፈቃድ ማመልከቻ መርምሮና ይግባኝ የተባለበትን ወገን አስቀርቦ መልስ በማሰጠት ይግባኙ በወቅቱ ሊቀርብ ያልቻለበት ምክንያት በቂ መሆኑን ካመነ፤ ይግባኝ ባዩ የይግባኝ አቤቱታውን በ፲ (አስር) ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት ይችላል፤



E. A complete copy of the proceedings and decision made by the complaint hearing council (including the complaint, response, and evidence) must be submitted by attaching a cover letter;

4. The person who lodges the appeal must verify, in accordance with the procedures of the civil code that the complaint is presented truthfully;

5. The council shall also accept appeals that are submitted through electronic means.

## 17. The Role of the Registrar

1. The Registrar shall verify whether an appeal submitted pursuant to Article 16 of this Regulation is complete according to the following criteria:

   A. whether the requirements of the appeal are met;

   B. whether the appeal is submitted within the time period that was specified as per the Proclamation and Regulation;

2. Without prejudice to paragraph (B) of Sub-Article 1 of this Article, any complaint which is submitted after the expiration of the appeal period must present an application for permission to open the appeal; if the council believes that the reason for failing to appeal on time is sufficient, upon examining the application and summoning the respondent to submit a reply, it may grant permission for the appellant to submit his appeal within 10 (ten) days;

፮. በቂ ባልሆነ ምክንያት ከቀጠሮ የቀረ ተከራካሪ ወገን ለሌላ ተከራካሪ ወገን ተመጣጣኝ ኪሳራ ከፍሎ ክርክሩ ሊቀጥል ይችላል፤

፯. የመስማት ሂደቱ የሚጀምረው ይግባኝ ባይ ነው፤ በመቀጠል መልስ ሰጪ በይግባኝ ባይ ክርክር ላይ በመንተራስ ክርክር ያቀርባል፤ በመጨረሻም ይግባኝ ባይ በቀረበው ክርክር ላይ ማስተባበያ ይሰጣል፤

፰. የጉባዔ ዳኛ ለውሳኔ ወይም ለውሳኔ ሐሳብ አሰጣጥ አስፈላጊ ነው ብለው ያመኑትን የማጣሪያ ጥያቄዎች ለግራ ቀኙ እንዲሁም ለባለሞያዎች ሰብሳቢው በሚሰጠው ቅደም ተከተል መሰረት ያቀርባሉ፡፡

## ፳፪. የችሎት ሥነ ሥርዓት አከባበር

፩. የችሎት ጸጥታ የሚያስከብሩ አካላት ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመነጋገር ፖሊስ ወይም ሥነ-ሥርዓት አስከባሪ ይመደባል፤

፪. ችሎት ላይ የሚገኙ ተሳታፊዎች የጉባዔውን አሠራርና የችሎቱን ሥነ ሥርዓት የማክበር ግዴታ አለባቸው፤ የጉባዔውን ሥራ ከሚያውክና ዓላማውን ከሚያደናቅፍ ድርጊት መቆጠብ ይኖርባቸዋል፤

፫. በችሎቱ ተሳታፊ ሆኖ የጉባዔውን ሥራ የሚያውክ ወይም የጉባዔው ዳኛና ሌሎች ተሳታፊዎች ላይ ያልተገባ ባህሪ የሚያሳይ ከሆነ ከችሎቱ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፫) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዚህ ደንብ መሰረት ተጠያቂ ይደረጋል፡፡



6. A party failing to appear at a hearing without sufficient cause may be ordered to pay reasonable costs to the other party and the proceeding may continue;
7. The hearing process shall begin with the appellant; then, the respondent shall present arguments based on the appellant's arguments; finally, the appellant may present a rebuttal;
8. Judges of the council may ask clarifying questions that they deem necessary for making a decision or recommendation to both litigating parties as well as for experts, following the respective order assigned by the chairperson.

## 22. Courtroom Decorum

1. Police or security officers shall be designated to maintain courtroom decorum in consultation with the relevant government body;
2. All participants present in court must observe the operations and order of the council; they must refrain from acts that disturb the activities of the council and obstruct its objectives;
3. Anyone present in court that disrupts proceedings or displays undue behaviour toward the judge of the council or other participants may be removed from the courtroom;
4. Without prejudice to Sub-Article (3) of this Article, appropriate legal actions may be taken under this Regulation when it deems necessary.

፪. ጉባዔው ለሚሰጣቸው ውሳኔዎችና ትእዛዞች ተፈጻሚነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፖሊስ ኃይል ይጠቀማል፡፡

**፳፮. <u>የእግድ ጥያቄ አወሳሰን</u>**

፩. ጉባዔው በቀረበለት የይግባኝ አቤቱታ ላይ ምርመራ አድርጎ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ዕግድ ሊሰጥ ይችላል፣

፪. በንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የእግድ ጥያቄ አቤቱታ የሚከተሉትን ማካተት ይገባል፡-

ሀ) የእግድ ጠያቂው ወገን ይግባኝ አቅርቦ መዝገቡ ተከፍቶ ፋይል መያዝ አለበት፤

ለ) እግዱ ባይፈቀድ ሊመለስ የማይችል ጉዳት የሚደርስ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፤

ሐ) እንደ አግባብነቱ ዕግዱ ባይሰጥ የሕዝብ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማስረዳት አለበት፤

፫. በዚህ አንቀጽ መሠረት እግድ የጠየቀውን አካል ጉባዔው አስፈላጊ ወይም በቂ ነው የሚለውን ዋስትና እንዲያሲዝ ሊያዘው ይችላል፡፡

**፳፯. <u>ያለመተባበርና ትዕዛዝ አለማክበር</u>**

በሌላ ሕግ ይበልጥ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፡-

፩. የጉባዔውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ያልፈጸመ ወይም እንዳይፈጸም እንቅፋት የሆነ፤ ወይም

፪. የጉባዔውን የዳኝነት ሥራ በአግባቡ እንዳይመራ ያሰናከለ ከብር ፲ሺ (አስር ሺህ) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።



2. The council may use police force when it deems necessary to enforce its decisions and orders.

**26. <u>Determination of Injunction Orders</u>**

1. The council may issue an injunction order until it examines an appeal submitted to it and pass a final decision on the thereof;
2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, an application for an injunction must meet the following conditions:

   A. The applicant seeking the injunction must have lodged an appeal and a file must be opened;

   B. Irreparable damage must be proven if the injunction is not granted;

   C. It must be demonstrated, as appropriate, that the interest of the public would be harmed if the injunction is denied.

3. The council may order the party that requests an injunction under this Article to post security when it deems necessary or sufficient.

**27. <u>Noncompliance and Contempt of Order</u>**

Unless punishable by a higher penalty under another law, any person who:

1. Fails to execute or obstructs the execution of an order or decision of the council; or
2. Impedes the proper administration of the judicial functions of the council, shall be punished with a fine not exceeding Birr 10,000.00 (Ten Thousand Birr).

**፴፩. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በደንብ ቁጥር ፴/ሺ.፱፻፺፬ ድንጋጌዎች መሰረት ተጀምሮ ያልተቋጨ ጉዳይ በተጀመሩበት አግባብ እልባት ያገኛል፡፡

**፴፪. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከ ሐምሌ ፭ ቀን/፪ሺ.፲፰ ዓም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፭ ቀን /፪ሺ.፲፰ዓ.ም**

**31. <u>Transitory Provisions</u>**

Cases initiated prior to the enactment of this Regulation under Regulation Number 30/2004 shall be resolved in accordance with the procedures under which they were commenced.

**32. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force as of this 12th day of July 2026.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of July 2026.**

**አዳነች አቤቤ ደሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**Adanech Abiebie Dessa**

**Mayor of Addis Ababa City**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

Sheet 1A 3/13/25 11:12:50 AM